

DV- 2015 እንዳይታለሉ!



ስለ ዲቪ እውነታውን ይረዱ!

ከዚህ በታች የተዘረዘሩት መረጃዎች በአዲስ አበባ አሜሪካን ኤምባሲ ለሚቀርቡ የዲቪ ቪዛ አመልካቾች ታስቦ የተዘጋጀ ነው፡፡

ለዲቪው ቪዛ ለማመልከት የሚያስፈልጉትን ቅድመ ሁኔታዎች ማሟላት የማይችሉ ከሆነ ቪዛውን አያገኙም፡፡ የአሜሪካን ኤምባሲ የቪዛ ቃለ መጠይቃቸው በአሜሪካ የቪዛ መኮንን ለተደረገላቸው የቪዛ አመልካቾች የከፈሉትን ገንዘብ የመመለስ ስልጣን የለውም፡፡

<u>ማመልከቻ፤</u> የዲቪ ማመልከቻዎ ተቀባይነት የሚኖረው በዚህ ድረ ገፅ በኩል www.dvlottery.state.gov ከመስከረም 21 እስከ ጥቅምት 23 ቀን 2006 ባለው ጊዜ ውስጥ ብቻ በኢንተርኔት በሚደረግ የዲቪ ማመልከቻ አቀራረብ አማካኝነት የማመልከቻ ፎርሙን ሞልተው ሲያቀርቡ ብቻ ነው፡፡ ከአንድ በላይ ማመልከቻ አቅርበው ቢገኙ ወዲያውኑ ከውድድሩ ውጪ ይሆናሉ፡፡

<u>የማመልከቻ ይዘትና ፎቶግራፍ፤</u> ለማመልከቻዎ ሃላፊነቱን የሚወስዱት እርስዎና እርስዎ ብቻ ነዎት፡፡ የዲቪ ማመልከቻዎ በሌላ ሰው ተሞልቶ ቢቀርብልዎት እንኳን ሙሉ ስምዎ፣ መረጃዎ እንዲሁም ፎቶግራፍ ከተሳሳተ ማመልከቻዎ ውድቅ ይሆናል፡፡

<u>መመረጥ፤</u> ቀደም ሲል ባቀረቡት የዲቪ ማመልከቻ አሸናፊ ሆነው እንደሆነ ለማወቅ ከሚያዝያ 23 ቀን 2006 ዓ.ም ወይም ከሚያዝያ ወር መጨረሻ 2006 ዓ.ም ጀምሮ በዚህ ድረገጽ ላይ በመግባት www.dvlottery.state.gov መመልከት ይችላሉ፡፡ በተጨማሪም የዲቪው አሸናፊ ሆነው ከተገኙ በቀጣይነት ማድረግ ስለሚገባዎት መመሪያ እና የቪዛ ቃለመጠይቅ የሚያደርጉበትን ቀንና ሰዓት ከዚሁ ድረ ገጽ ላይ ማግኘት ይችላሉ፡፡

<u>ክፍያ:</u> ዲቪ ሎተሪ ለማመልከት ምንም ዓይነት ክፍያ የለውም፡፡ በዲቪ ፕሮግራም ውስጥ ለመሳተፍ (ለማመልከት) ጠበቃ ወይም ጉዳይ አስፈፃሚ አያስፈልግም፡፡ ክፍያ የሚያስፈልጋቸው የዲቪ አሸናፊ የሆኑ አመልካቾች ብቻ ሲሆኑ ክፍያውም በቃለ መጠይቅ ቀጠሮ ቀን በኤምባሲው ቅጥር ጊቢ ውስጥ የሚፈፀም ይሆናል፡፡ የዲቪ አሸናፊ ከሆኑ በምንም ዓይነት መልኩ ለቃለ መጠይቅ በተቀጠሩበት ቀን ወደ ኤምባሲው ከመምጣትዎ በፊት ምንም ዓይነት ክፍያ እንዳይፈፅሙ፡፡

<u>ስፖንሰር (Sponsor)፤</u> ለዲቪ ቪዛ ብቁ ለመሆን ስፖንሰር አያስፈልግም፡፡

<u>ጋብቻ፤</u> ለዲቪ ቪዛ ብቁ ለመሆን የግድ የዲቪው ዕድለኛ ከሆነ በኋላ ትዳር መመስረት አያስፈልግም፡፡ ትክክለኛ ያልሆነ /ሃሰተኛ ጋብቻ/ ፈፅመው የሚቀርቡ ከሆነ ከዚህ በኋላ ባለው የህይወት ዘመንዎ ሁሉ ወደ አሜሪካ አገር እንዳይገቡ ይታገዳሉ፡፡

ቤተሰብ፤ በመጀመሪያ በሚያቀርቡት የዲቪ ማመልከቻዎ ላይ ባለቤትዎንና እድሜያቸውን ከ21 ዓመት በታች የሆኑ ግን ያላገቡ/ትዳር ያልያዙ/ ልጆችዎን ሁሉ በማመልከቻዎ ላይ አጠቃለው ሊያስመዘግቡ ይገባዎታል፡፡ ከላይ የተጠቀሱትን የቤተሰብ አባላት በማመልከቻዎ ላይ ሳያካትቱ መቅረት የዲቪውን ቪዛ እንዳያገኙ ያደርግዎታል፡፡

ትምህርት፤

የኢትዮጵያ መንግስት የሥርዓተ ትምህርት ለውጥ አድርጓል፡፡

በዚህ የተነሳ በርካታ በሙያ ስልጠና /Technical and Vocational/ ላይ የነበሩ ወይም የሚገኙ ተማሪዎች ለዲቪ ፕሮግራም ብቁ አይሆኑም፡፡ ለዲቪው ፕሮግራም ብቁ ለመሆን አመልካቾች ለአስራ ሁለት ዓመታት የተሰጡ መደበኛ ትምህርቶችን የተከታተሉ እና የጨረሱ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

ስለዚህ በዲቪው ብቁ ለመሆን ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት ቢያንስ አንዱን ሊያሟሉ ይገባቸዋል፡፡

ESLCE - የቀድሞን የ12ተኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና ወስደው በአምስት ትምህርቶች ከA-D ያለውን ውጤት ያስመዘገቡ ወይም

የ10ኛን ክፍል ብሔራዊ ፈተና ወስደው በተጨማሪ የ3 ዓመታት የሙያ ስልጠና ወስደው ያጠናቀቁና (10+3) በሶስቱም የስልጠና ዓመታት ውስጥ ሒሳብ፣ እንግሊዝኛና የስነ ዜጋ ትምህርቶችን የተከታተሉ ወይም

ከኢትዮጵያ የውትድርና አካዳሚ የተመረቁ ሊሆኑ ይገባቸዋል፡፡

የሥራ ልምድ፤ የሥራ ልምድ ግንዛቤ ውስጥ የሚገባው አመልካቾች በትምህርት መመዘኛ ብቁ ሆነው ሳይገኙ ሲቀሩ ነው፡፡ ብቁ የሥራ ልምድ ተብሎ ሊወሰድ የሚችለው ባለፉት 5 ዓመታት ውስጥ ሶስት ዓመት የኮሌጅ ስልጠና በሚወስድ የሥራ አይነት ቢያንስ ለሁለት ዓመታት የሰራበትን የሥራ ልምድ አመልካቹ ማቅረብ ሲችል ነው፡፡ በትምህርት ወይም በአሜሪካን የውጪ ጉዳይ ቢሮ የተመሰከረለትና በዚህ ድረ ገፅ ውስጥ www.online.oretcenter.org የተካተተ ብቁ የሚያደርግ የሥራ ልምድ ከሌልዎ ለዲቪ አያመልክቱ፡፡

ኢ-ሜይል: የአሜሪካን መንግስት በፍፁም የዲቪ አሸናፊነትዎን የሚገልፅ መልዕክት በኢ-ሜይል አይልክም፡፡ የሎተሪው አሸናፊ መሆንዎን የሚገልፅ መረጃ ማግኘት የሚችሉት በዚህ ድረ ገፅ ላይ በመመርኮዝ ብቻ ይሆናል፡፡ በኢ-ሜይል የሚደርስዎ አሸናፊነትዎን የሚገልፅ መልዕክት ሁሉ የማጭበርበሪያ መልዕክት ነው፡፡

ማስረጃዎች፤ የተጭበረበሩ ሀሰተኛ የሆኑ ማንኛውንም ዓይነት ማስረጃዎች /Documents/ ለኤምባሲው እንዳያቀርቡ፡፡ ሃሰተኛ ዶክመንቶችን ማቅረብ ወዲያውኑ ከውድድሩ እንዲታደጉ ያደርግዎታል፡፡

ፖስታ፤ የዲቪ 2015 ፕሮግራም ከፖስታ ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት የለውም፡፡ በፖስታ የሚላኩ ማናቸውም የዲቪ ማመልከቻዎች ትክክለኛነት የላቸውም፡፡ የአሜሪካን መንግስት በምንም ዓይነት መልኩ የዲቪ አሸናፊነትዎን የሚገልጽ ደብዳቤ በፖስታ ቤት አይልክም፡፡ አሸናፊ መሆንዎን የሚገልጽ መረጃ ማግኘት የሚችሉት ከዚህ ድረ ገፅ ላይ በመሄድ ብቻ ነው፡፡ www.dvlottery.state.gov ማናቸውም በፖስታ የሚመጡ ከዲቪ ጋር የተያያዙ የሚመስሉ መልዕክቶች የማጭበርበሪያ መልዕክቶች እንደሆኑ ልብ ይበሉ፡፡

ቃለ መጠይቅ፤ የዲቪ አሸናፊ ከሆኑ ከታች የተጠቀሱትን ማስረጃዎች /Documents/ በቃለ መጠይቅ ቀጠሮዎ ቀን ይዘው እንዲቀርቡ ይጠበቅብዎታል፡፡ በእንግሊዘኛ ያልተዘጋጁ ማናቸውንም ማስረጃዎች /documents/ በእንግሊዘኛ ተተርጉመው መቅረብ አለባቸው፡፡

አስፈላጊ ማስረጃዎች፤

- ፓስፖርት
- የልደት ማስረጃ
- የጋብቻ ማስረጃ (ያገቡ ከሆኑ)
- የፍቺ ሞት ማስረጃ (ፍቺ ሞት የነበረ ከሆነ)
- የህክምና ማስረጃ (ከተፈቀደለት የህክምና ማዕከል)
- የፖሊስ ወረቀት
- የፖሊስ ወረቀት ከሌላ ሃገር /ከ 16 ዓመቱ/ቷ ጀምሮ/ጀምራ የቪዛ አመልካቹ/ አመልካችዋ ከትውልድ ሃገራቸው ውጪ ከ1 ዓመት በላይ ኖረው የነበረ ከሆነ/
- ዲፖርቴሽን ማስረጃ /Deportation Paper/
- የፍርድ ቤት /የወህኒ ቤት ወረቀት/
- የውትድርና አገልግሎት ማስረጃ
- አስፈላጊ የሆኑ የትምህርት ማስረጃዎች /በትምህርት ሚ/ር የሀገር አቀፍ ፈተናዎች ቢሮ/ የተረጋገጠ ወይም የሥራ ልምድ
- ሁለት ፎቶ 5 ሳ.ሜ. በ5 ሳ.ሜ. የሆነ
- የዲቪ ቪዛ አገልግሎት ክፍያ 330 የአሜሪካን ዶላር ወይም በጊዜው የምንዛሪ ተመን የኢትዮጵያ ብር /በጊዜው ባለው ምንዛሪ/